# ሽርክት ፖለቲካ

በወያኔ ተንኮል ፤ በጎጠኞች ደባ
ትንሹም ትልቁም ፤ ሆነና ሰለባ
ፓርቲው ፤ እንደ አሜባ ፤ ዘሩ እየተራባ
ክፍፍል ሲፈጠር ፤ በረባ ባልረባ
ጦርነቱ ሲጦፍ ፤ ጭቃ እየተቃባ
እንደ ተላላፊ ፤ በፓልቶክ ተጋባ
ወያኔ ዘፈነ ፤ አለ ፤ ጉሮ ወሸባ
አኮላሸው ሁሉን ፤ አደረገው ሸባ ።

ፓርቲውም ፤ ፓልቶኩም ፤ እየቀባጠሩ
ለጊዜያዊም ቢሆን ፤ ህብረት እንዳይጠሩ
መንገድ እንደመጥረግ ፤ አጥር እያጠሩ
በራስ ላይ ዘመቻ ፤ አድሜ እያሳጠሩ
መሞት በማግስቱ ፤ እንደተፈጠሩ ።

በፓልቶክ ታዳሚ ፤ ሽርክት ፖለቲካ
ለወሬት ለመታት ፤ ሲበጠር ሲከካ
መቋጫ የሌለው ፤ የወሬ ትረካ
ግራ ቀኝ ሲዘል ፤ ሁሉን ሲነካካ
እያንቦጫረቀ  ፤ ሲያላዝን ሲያቦካ
ዛሬም ይደለቃል ፤ ደርሶለት ፋሲካ
በወያኔው ምርጫ ፤ ወያኔን ሊተካ ።

አርባራቱን ታቦት ፤ ጽላት ተመስሎ
አርባራት የፓልቶክ ፤ በሰልፍ ተኮልኩሎ
እንደ ችርቻሮ ፤ መደብ ተከፋፍሎ
የጭፍኑ መንገድ ፤ ከውሩ ተሽሎ
እርስ በርስ ይናጫል ፤ አልግባባ ብሎ
አንዱ አንዱን ፤ ይነክሳል ፤ ሊበላው ዘንጥሎ ።

ታዛቢው ... February, 26, 2010